በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፈ ነህምያ - ክፍል ፫


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**መስከረም ፳፱ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

- ዛሬ የአመራር ድኅነትና ችግር እያጠቃት ባለችው ዓለማችን በተለያዩ ጎኖች የሚታዩ የአመራር ክፍተቶች አሉ። ከዚህም የተነሣ በእያንዳንዱ ቤት፣ ትዳር፣ … የመሪዎች አስፈላጊነት ጉልህ እየሆነ ነው።
- ወንዶችም ሆን ሴቶች፣ ድሆችም ሆን ባለጠጎች እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የምንመራ መሪዎች እንድንሆን ይፈልጋል። እኛም ይህን የመምራት ኃላፊነት እንዴት መወጣት እንዳለብን መረዳት ይጠበቅብናል።
- መሪዎች የተፈጥሮ ብቻ ሳይሆኑ የተማሩና የተሠሩም ጭምር ናቸው። ለመሪነት እንዴት እንደምንሠራ ታላቅ መሪ እንዴት እንደምንሆን ተምረን መረዳት እንችላለን። ምናልባት አይመለከተኝም ብለን ካልተውን፣ ዝቅ ያለ በራስ የመተማመን ችግር ውስጥ ወድቀን ካልተውነው በቀር ወይም እግዚአብሔር የሰጠን ይህ ኃላፊነት አይመለከተኝም ካላልን በቀር መሪዎች የምንሆንበትን ዕውቀት መቅሰምና መማር እንችላለን።
- ባለፉት ሳምንታት መጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ አንድን ተመልክተናል። በዚሁ መሠረት መሪ የሚያስፈልጉትን አራት ቁልፍ ነገሮች (Essentials/Qualities) ተመልክተናል።
  1. መሪ ከሁሉ በፊት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ቅድሚያ ይሰጣል:: (Recognition of the Need)
  2. መሪ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በግሉ የሚያሳስቡት (ስለ ቅጥሮቹ መፍረስ እንዳለቀሰ እንደ ነህምያ) ሰው ነው:: (Have concern for the Need)
  3. ከልቡ የሆነ መሪ ችግሮቹን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባቸዋል።(Putting the Need before God)
  4. ከልቡ የሆነ መሪ አስፈላጊውን ነገር በራሱ ለማሟላት (ከኔ ምን ይጠበቅብኛል?) በማለት ይነሳሳል ራሱን የመፍትሔ አካል ያደርጋል። (Available to fulfill the need)
- ነህምያ በእስራኤል ነቢይ፣ ካህን፣ ወይም ሌዋዊ አልነበረም፤ ብዙ ፍርሐት የነበረበት ንጉሥ አገልጋይ ነበር። የዓመት ፈቃድ ወስዶም ሆነ ለመውሰድ እንኳ አስቦ አያውቅም።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

- በሕይወታችሁ ወይም በዙሪያችሁ የማትቆጣጠሩት ነገር እያለም እንኳ መሪ መሆን ይቻል ይሆን? ምንም ማድረግ የማትችሉ ልጆች እንጂ ወላጆች ላትሆኑ ትችላላችሁ፣ ተቀጣሪ እንጂ ቀጣሪ ላትሆኑ ትችላላችሁ? ይህም ሆኖ ግን መምራት እንችላለን? ነህምያ ከኃላፊነቱ ክብደት የተነሣ አፉን ከፍቶ መጠየቅ የሚችል አልነበረም።
- ዮሴፍ እንደተገዛ ባሪያ ያለ ሰው ቢሆንም መልካም መሪ ነበር፤ ሙሴም እንዲሁ። ሙሴ በወንዝ ዳር ተጥሎ ምንም ሥልጣን የሌለው ሰው ከመሆን ተሀሥቶ መሪ ለመሆን የበቃ ነው። መሪነት ከሥልጣን ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም።
- ነህምያ የእስራኤልን ሕዝብ የሚመራበት ሥልጣን አልነበረውም፤ በቤተ መንግሥቱ እንኳ የሚታዘዘውን ከመፈጸም በቀር በአገሩ ጉዳይ እኛ የምንጠብቀውን ዓይነት ውሳኔ የመወሰን ሥልጣን አልነበረውም።
- አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ፣ ሥልጣን፣ ወዘተ ስለሌለን መምራት አንችልም ይላሉ ነገር ግን በዚህ ዓይነት ሁኔታም ውስጥ ሆነን መሪ በመሆን ታላላቅ የእግዚአብሔር ዓላማዎችን ማሳካት እንችላለን።
- ነህምያ ያደረገውን ተመልከቱ። የከተሞችዋ ቅጥሮች 800 ማይል ርቃ በምትገኘው ኢየሩሳሌም ፈርሰው ነበር። ታዲያ ለአንድ ሳምንት ፈቃድ ጠይቆ ቢሄድ መንገዱ ራሱ ጊዜውን ይጨርሰዋል፤ ንጉሡም ደህንነት ስለማይሰማው በቀላሉ አይፈቅድለትም። ታዲያ ምን ማድረግ ይችላል?
- ለኢየሩሳሌምና ለወገኖቹ በዚህ ወቅት ምን ሊያደርግላቸው ይችላል? ሚስት፣ ቤተሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ ነህምያ ያሰበውን እንዲያሳካ ሊያሳድሩ የሚችሉት ተጽእኖ አለ ይሆን? ነህምያ ስለዚህ ጉዳይ እጅግ ውብ የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል - ምክር አግኝቶ አምኖ በመቀበል ተጠቅሞበታል።
-

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፫

- ‹‹የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል።›› **ምሳ 21፡1፡፡** አዎ በንጉሥ ፈቃድ ሥር ነኝ ነገር ግን እግዚአብሔር ንጉሡን ልቡኑም ይቆጣጠረዋል፡፡ ንጉሥ አንድ ነገር እንዲወስንልን ልንጸልይ እንችላለን፤ ነገር ግን አንድ ነገርን ማድረግን እንዲወድ ወይም ልጆቻችን/የትዳር አጋራችን የምንወደውን አንዳች ነገርን ማድረግ እንዲወዱ እንጸልይላቸዋለን?
- በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን መቆጣጠር እንችላለን? እግዚአብሔር ግን ይቆጣጠራቸዋል፣ ልባቸውንም ይቆጣጠራል፡፡ በእኛም ልብ ያለውን መሻት እንዲፈጽሙ እግዚአብሔር ያበቃቸዋልና ነህምያ በምዕራፍ አንድ መጨረሻ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ጸሎትን ጸለየ፡፡ ‹‹ጌታ ሆይ፥ ጆሮህ የባሪያህን ጸሎት፥ ስምህንም ይፈሩ ዘንድ የሚወድዱትን፥ የባሪያዎችህን ጸሎት ያድምጥ ዛሬም ለባሪያህ አከናውንለት፥ በዚህም ሰው ፊት ምሕረትን ስጠው። እኔም ለንጉሡ ጠጅ አሳላፊው ነበርሁ።›› **ነህ 1፡11፡፡**
- ነህምያ ይህን ጸሎት ከጸለየ በኂላ ለአራት ወራት ጠበቀ፤ ምንም አልሆነም፡፡ እግዚአብሔር ሆይ በንጉሡ ፊት ሞገስን ስጠኝ ብሎ ጸለየ ነገር ግን ምንም ነገር ሲሆን አላየም፡፡ ነህምያ ምዕራፍ 2 እንመልከት፡፡
- ‹‹ በንጉሡ በአርጤክስስ በሀያኛው ዓመት በኒሳን ወር የወይን ጠጅ በፊቱ በነበረ ጊዜ ጠጁን አንሥቼ ለንጉሡ ሰጠሁት። ቀድሞ ግን በፊቱ ያለ ኃዘን እኖር ነበር። ንጉሡም። ሳትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብ ኀዘን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም አለኝ። እጅግም ብዙ አድርጌ ፈራሁ።›› **ነህ 2፡1-2፡፡** አዎ ቢያዝንም ከመጋረጃ ጀርባ ሊያለቅስ ይችላል እንጂ በንጉሡ ፊት አይገልጠውም ነበር፤ አሁን ግን መደበቅ አቃተው፡፡ አራት ወር ሙሉ ሲጸልይበት፣ ደብቆም በራሱ ያለቅስበት የነበረውን ነገር አሁን ግን መሰወር ተስኖት ንጉሡ አወቀበትና ምን ሆነሃል? ብሎ ጠየቀው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

- ንጉሡ ሲያውቅበትም እንጀራውን እንዳያጣ እጅግ ፈራ፡፡ ምክንያቱም መጠጥ አቅራቢ (የመጠጥ ቤት አስተናጋጅ) አጫዋች መሆን ይጠበቅበታልና፤ የተከሰከሰ ፊት ይዞ ማስተናገድ እንጀራን ያሳጣል፡፡
- ነህምያ ምን ሆነሃል ተብሎ ሲጠየቅ የነበረውን ሁኔታ ፈራሁ ሲል ጽፎልናል፤ ታማኝ ሰው ነበርና፡፡
- መሪ እንዴት አድርጎ ደካማ ጎኑን (ፍርሐቱን) መቀበል እንዳለበት ያውቃል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተጻፉ እያንዳንዳቸው ቃላት ለመሪዎች ወርቃማ ቃላት ናቸው፡፡
- ‹‹ንጉሡንም። ንጉሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለ ምን አይዘን? አልሁት። ንጉሡም። ምን ትለምነኛለህ? አለኝ። እኔም ወደ ሰማይ አምላክ ጸለይሁ።›› ***ነህ 2፡3-4፡፡***
- ነህምያ ሲጠየቅ ምላሽ ሰጠ፡፡ ምን እንዳደርግልህ ትወዳለህ? ሲባልም መልስ ከመስጠቱ በፊት ጸለየ፡፡
- አሁን የጸሎቱን ምላሽ ሊያገኝ ነው፤ አሁን እግዚአብሔር ሊመልስለት ነው፡፡ ከአራት ወር በኋላ የንጉሡ ልብ ታዘዘ፡፡ ንጉሡ ሲጠይቀው ነህምያ ወዲያው ምላሽ መስጠት ይችል ነበር፡፡ ይቅርታ ዝም ብዬ ነው፣ የግሌን ጉዳይ ወደ ሥራ ገበታ ይዤ ስለቀረብኩ ይቅርታ፣ … ብሎ ወዲያው ምላሽ መስጠት ይችል ነበር፡፡
- የሚያስደንቀው ግን ነህምያ ሲጠየቅ ስለሚሰጠው ምላሽ ተዘጋጅቶ ነበር፤ ይህም ለአንድ መሪ የሚያስፈልገው ቁልፍ ነገር ነው፡፡

5. ***መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው፡፡***

- እግዚአብሔር ለጸሎታችን ምላሽ ሲሰጠን ስለምንሠራው ነገር ዝግጅት አለን፣ ዕቅዶችስ እናዘጋጃለን?
- ‹‹የሰው ልብ መንገዱን ያዘጋጃል እግዚአብሔር ግን አካሄዱን ያቀናለታል።›› ***ምሳ 16፡9፡፡*** እንዳለ እግዚአብሔር የሰውን እቅድና ዝግጅት ያደንቃል፡፡
- መዘጋጀት የእኛ ድርሻ ነው፤ መዘጋጀት ወይም ማቀድ ከእምነት ጋር ምንም ጠብ የለውም፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

5. ***መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው…***

- **እኛ እንዳቀድነው ነገሮች ሁሉ ይሄዳሉ ማለት አይደለም፤ እኛ እናቅድ እንጂ እግዚአብሔር አስተካክሎ ያሳካቸዋል፡፡**
- **የሰማይ መስኮት (ደጅ) ቢከፈትልን ምን እንደምንጠይቅ አዘጋጅተናል? ቅዱስ ገብርኤል (ቅዱስ ሚካኤል) ቢላኩና ቢያነጋግሩን ምን እንደምንጠይቃቸው አዘጋጅተናል? ነህምያ የምትፈልገውን ጠይቅ ሲባል** ‹‹ንጉሡንም። ንጉሡን ደስ ቢያሰኝህ፥ ባሪያህም በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ፥ እሠራው ዘንድ ወደ ይሁዳ ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ አልሁት።›› ***ነህ 2፡5፡፡*** **በማለት መሄድና መሥራት እፈልጋለሁ ብሎ ጠየቀ፡፡**
- ‹‹ ንግሥቲቱም በአጠገቡ ተቀምጣ ሳለች ንጉሡ። መንገድህ እስከ መቼ ድረስ ይሆናል? መቼስ ትመለሳለህ? አለኝ። ንጉሡም ይሰድደኝ ዘንድ ደስ አለው እኔም ዘመኑን ቀጠርሁለት።›› ***ነህ 2፡6፡፡*** **እንዳለ ንጉሡ መቼ መሄድ ትፈልጋለህ?፣ እስከ መቼ ትቆያለህ?፣ መቼ ትመለሳለህ? ብሎ ጠየቀው፡፡**
- **ነህምያ ተዘጋጅቶ ነበር፤ ባይዘጋጅ ግን ይህ ዕድል ተመልሶ አይመጣም ነበር፡፡ በንጉሡ ፊት ካለመዘጋጀቱ የተነሣ ‹‹ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እፈልጋለሁ ብዙ ቀንም አይፈጅብኝም›› ቢል ያልተቆረጠው ነገሩ በንጉሥ ፊት ተቀባይነት የሚያገኝ አይሆንለትም ነበር፤ እንዲህ ያለ መልስ ከመሪ የሚጠበቅ አይደለምና፡፡**
- **በመቀጠልም** ‹‹ ንጉሡንም። ንጉሡ ደስ ቢለው፥ እስከ ይሁዳ አገር እንዲያደርሱኝ በወንዝ ማዶ ላሉት ገዦች ደብዳቤ ይሰጠኝ በቤቱም አጠገብ ላለው ለግንብ በሮች፥ ለከተማውም ቅጥር፥ ለምገባበትም ቤት እንጨት እንዲሰጠኝ ለንጉሡ ዱር ጠባቂ ለአሳፍ ደብዳቤ ይሰጠኝ አልሁት። ንጉሡም በእኔ ላይ መልካም እንደ ሆነችው እንደ አምላኬ እጅ ሰጠኝ።›› ***ነህ 2፡7-8፡፡*** **አለ፡፡ ይህም አንደኛ በቀላሉ ማለፍ እንድችል ቀዩን ፓስፓርት ስጠኝ አለ፤ ሁለተኛም በምሄድበት የምቀይበት ቤት እንድሠራ እንጨቱ ይሰጠኝ አለ፡፡ ረስቶ ሄዶ ፓስፖርቴን ረስቸዋለሁ፣ ደብዳቤ አልያዝኩም አላለም፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

5. <u>*መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው…*</u>

- እግዚአብሔርም ለነህምያ ጸሎት መልስ ሰጠው፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች ሳይዘጋጁ አምነናል በሚል ብቻ ዘለው ወደ *ሥራ* ይገባሉ፤ ይህም ስንፍና ነው፡፡ ወደ *ሥራ* መግባት ቀላል ቢሆንም ዝግጅት(ዕቅድ) ግን ከባድ ነው፡፡
- ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ወደ ሰንበት ት/ቤት ኮርስ ትምህርት፣ ወደ ተለያዩ ጉባኤያት መግባት ቀላል ነው፡፡ ነገር ግን ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ መጸለይ፣ በተመስጦ ማሰብ… ግን ቀላል አይደለም፡፡
- አንድን *ሥራ* ስንሠራ በፍጥነት ስለ *መሥራት* ነው ወይስ በትክክል ስለ *መሥራታችን* ነው የምናስበው?
- የምናገለግለው ብዙ *ሥራዎችን* በአንድ ጊዜ *መሥራት* በምንችልበት ሁኔታ ነው ወይስ እጅግ በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል በምንችልበት መንገድ ተዘጋጅተን ነው?
- አስቀድሰን ደስ ብሎን፣ ተምረን ተሰብከን ተጠቅመን መመለስ እንፈልጋለን? እንግዲያውስ አስቀድመን እንዘጋጅ፡፡ የታላላቅ መሪዎች ማንነት ፈርጡ ማቀድና መዘጋጀት ነውና፡፡
- ሳንዘጋጅ ዘለን ወደ አገልግሎት፣ ወደ ጸሎት፣ ወደ ቅዳሴ… ወዘተ ከመግባት መቆጠብ አለብን፡፡ ለእግዚአብሔር ጊዜ በመስጠት በመዘጋጀት እናድርገው እንጂ፡፡
- አሁን ሁሉ ተስታክሎአል ነህምያ ለመሄድ ዝግጁ ነው፡፡ ሰይጣን ግን በነህምያ ዝግጅት ደስተኛ አልነበረም፡፡
- ‹‹በወንዙም ማዶ ወዳሉት አለቆች መጥቼ የንጉሡን ደብዳቤ ሰጠኋቸው ንጉሡም ከእኔ ጋር የሠራዊቱን አለቆችና ፈረሰኞች ሰደደ። ሖሮናዊውም ሰንባላጥና ባሪያው አሞናዊ ጦብያ ለእስራኤል ልጆች መልካምን ነገር የሚሻ ሰው እንደ መጣ በሰሙ ጊዜ እጅግ ተበሳጩ።›› <u>*ነህ 2፡9-10፡፡*</u> እንዳለው ለእስራኤል ጎረቤት ሆነው የሚኖሩ እነዚህ ‹‹ሌላ *ሥራ*›› ስላላቸው ደስተኞች አልነበሩም፡፡ ኢየሩሳሌም መልሳ ጠንካራ እንድትሆን፣ ንግድዋም እንዲሰፋ አይፈልጉም ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን *ሥራ* እንዳይሠራ ነህምያን ሊያቆሙትና ሊያደናቅፉት ተዘጋጁ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፫

5. <u>*መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው…*</u>

- *የእግዚአብሔርን ሥራ የምንሠራ ከሆንን ተቃውሞና ነቀፋ ይመጣ ዘንድ የግድ ነው። የእግዚአብሔርን ሥራ ስንሠራ ተቃውሞና ነቀፋ ካልገጠመን አንድ እየሠራነው ያለ ስህተት እንዳለ እርግጠኞች እንሁን፤ የርሱን ሥራ ስንሠራ እነዚህ ይገጥሙን ዘንድ የሚገባ ነውና።*
- *መልካም መሪም ለተቃውሞውና ለነቀፋው ዝግጁ ነው።*
- *ነህምያ* ‹‹ወደ ኢየሩሳሌምም ደረስሁ፥ በዚያም ሦስት ቀን ያህል ተቀመጥሁ።›› <u>***ነህ 2፡11፡፡***</u> *አለ። ሦስቱን ቀን ምን እንደሚሠራ አያውቅም፣ እግዚአብሔር ሊመራው፣ ሊያመለክተው፣ በሩንም ሊከፍትለት ይገባልና ሦስት ቀን ቆየሁ አለ። ይህንም ሱባኤ - አርምሞ (ጽሙና) እንለዋለን።*
- *ለአንድ ጉዳይ ምላሽ ስናጣ ወደ ክፍላችን ገብተን ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዘግተን (ኢንተርኔት ሳንጠቀም፣ ቻት ሳናደርግ፣ ስልክ ሳናወራ… ዝም ብለን ዘግተን) እንቆይ።*
- *የመሪዎች ጥልቅ ንግግሮቻቸው የሚወለዱት ከጽሙና ነው፣ ግልጽ ዕቅዶቻቸውና ራእዮቻቸውም የሚመነጩት ከአርምሞ ነው። በሕዝብ ዘንድ የሚጎናጸፉት ክብር የሚገኘውም ከዚሁ ከመሰወሪያ ቦታቸው ነው። እኛ ወደ ተዘጋጀንበት ተግባር ከመግባታችን በፊት ሦስት ቀናት ቢኖሩን በነዚህ በሦስት ቀናት ምን እናደርጋለን?*
- *ነህምያ* ‹‹በሌሊትም ተነሣሁ፥ ከእኔም ጋር አያሌ ሰዎች ነበሩ እግዚአብሔርም ለኢየሩሳሌም አደርገው ዘንድ በልቤ ያኖረውን ለማንም አላስታወቅሁም ተቀምጬበት ከነበረው እንስሳ በቀር ከእኔ ጋር ምንም እንስሳ አልነበረም።›› <u>***ነህ 2፡12፡፡***</u> *አለ።*
- *መሪዎች ብዙ አይናገሩም። ነገሮችን ያሰናዳሉ፣ ይጸልያሉ፣ በቅደም ተከተል ያዘጋጃሉ፣ በመቀጠልም ግልጥ ያደርጉታል። እንሞክራለን፣ እናስባለን ወዘተ አይሉም፣ ተዘጋጅተው ጀምረው ጠንክረው ይገፋሉ።*

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፫

5. **መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው…**

- ‹‹በሸለቆውም በር ወጣሁ፥ ወደ ዘንዶውም ምንጭና ወደ ጉድፍ መጣያው በር ሄድሁ የፈረሰውንም የኢየሩሳሌምን ቅጥር፥ በእሳትም የተቃጠሉትን በሮችዋን ተመለከትሁ። ወደ ምንጩም በርና ወደ ንጉሡ መዋኛ አለፍሁ ተቀምጬበትም የነበረው እንስሳ የሚያልፍበት ስፍራ አልነበረም። በሌሊትም በፈፋው በኩል ወጥቼ ቅጥሩን ተመለከትሁ ዘወርም ብዬ በሸለቆው በር ገባሁ፥ እንዲሁም ተመለስሁ። ሹማምቱ ግን ወዴት እንደ ሄድሁ፥ ምን እንዳደረግሁም አላወቁም ነበር ለአይሁድና ለካህናቱ፥ ለታላላቆችና ለሹማምቱም፥ ሥራም ይሠሩ ለነበሩት ለሌሎች ገና አልተናገርሁም ነበር።›› ***ነህ 2፡13-16፡፡***
- ***ሥራውን የሚሠሩት ሰዎች እንኳ ምን እንዳደረገ አያውቁም ነበር፡፡ ነገሮችን በጥልቀት ልካቸውንና መጠናቸውን መረመረ፡፡ ይህ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አስቡት፡፡ ሰዎች ይህንን ለመሥራት ምን ያህል መሣሪያ ያስፈልጋቸዋል፤ ይህ ሥራ የሚታይ ነው ወይስ የማይታይ? ነህምያ ነገሮችን ሁሉ መረመራቸውና ቀጥሎ ነገራቸው፡፡*** ‹‹እኔም። እኛ ያለንበትን ጕስቍልና ኢየሩሳሌም እንደ ፈረሰች፥ በሮችዋም በእሳት እንደ ተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ አልኋቸው።›› ***ነህ 2፡17፡፡***
- **እነርሱን ለማነሳሳት ምን አደረገ? ደመወዝ እጨምርላችኋለሁ አላለም፡፡ የተሻለ ሕይወት ትመራላችሁ… ዝም ማለታችሁ ያሳፍራል… አላላቸውም፡፡ ‹‹አሁን እንዲህ እናድርግ›› ብሎ አነሳሳቸው፡፡ የሚያሳፍረውን ብቻ አንስቶ ወቃሽ ብቻ አልሆነም፡፡**
- **‹‹እኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንሁን፣ ኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ከተማ ትሁን፣ መሳለቂያ ከመሆን ነጻ እንውጣ፡፡›› በማለት ሕዝቡን ለሥራ አነሳሳቸው፡፡** ‹‹የአምላኬም እጅ በእኔ ላይ መልካም እንደሆነች፥ ንጉሡም የነገረኝን ቃል ነገርኋቸው። እነርሱም፦ እንነሣና እንሥራ አሉ። እጃቸውንም ለበጎ ሥራ አበረቱ።›› ***ነህ 2፡18፡፡***
- **ብዙ መሪዎች በዚህ መንገድ ሕዝቦቻቸውን ማነሳሳት ይሳናቸዋል፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

5. ***መሪ ተዘጋጅቶ የሚራመድ ነው…***

- **ይሁን እንጂ** ‹‹ሖሮናዊውም ሰንባላጥ፥ ባሪያውም አሞናዊው ጦብያ፥ ዓረባዊውም ጌሳም በሰሙ ጊዜ በንቀት ሳቁብን፥ ቀላል አድርገውንም። ይህ የምታደርጉት ነገር ምንድር ነው? በውኑ በንጉሡ ላይ ትሸፍቱ ዘንድ ትወድዳላችሁን? አሉ።›› ***ነህ 2፡19*** **እንዳለ መነሳሳታቸው ብቻ ግብ አልነበረም፡፡ ተቃውሞውና ነቀፋውም ቀጠለ እንጂ፡፡**
- **ነህምያም** ‹‹እኔም መልሼ። የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን እናንተ ግን በኢየሩሳሌም እድል ፈንታና መብት መታሰቢያም የላችሁም አልኋቸው።›› ***ነህ 2፡20*** **እንዳለን አላቸው፡፡**
- **ሥራው ከእኔ አይደለም፤ እኔ አላመነጨሁትም፣ አላሰብኩትም… እግዚአብሔር ነው አላቸው፡፡ ሰዎች ምንም ቢሆኑ ይህን ከእግዚአብሔር የሆነን ነገር ሊቋቋሙት አይችሉምና ‹‹እግዚአብሔር እኔን ተጠቅሞ እናንተን ሊባርክ ይህንን አደረገ፡፡›› አላቸው፡፡**
- **በዛሬው ትምህርታችን *በአንድ ጉዳይ የሰውን ልብን እንዴት መለወጥ እንደሚቻል - እግዚአብሔር የንጉሡን ልብ እንዴት እንደለወጠ በመገንዘብ፣ እግዚአብሔር እስኪያደርግልን ድረስ እየጠበቁ ስለመጸለይ አስፈላጊነት፣ እምነት ከዕቅድ ጋር እንደማይጣላና የእግዚአብሔርን ሥራ ስንሠራ ተቃውሞና ነቀፋ ስለሚኖር ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብን* ስለሚነግሩን *አራት ፍሬ ነገሮች* ተምረናል፡፡ የእግዚአብሔርን ራእይ የሚያሳኩ ሰዎችም እነዚህም ገንዘብ በማድረግ ተስፋ ባለመቁረጥ ይራመዳሉ፡፡እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ለመራመድ ሁላችንንም የበቃን ያድርገን፡፡ አሜን!!!**

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org